# ህወሃት - በትግራይ ሕዝብ ዙርያ የበቀለ የሙስና እንቧጭ ነው።
# ይድረስ ለአርበኛውና ኃይማኖተኛው የትግራይ ሕዝብ

ጣና ጎጃምና በጌምድር ድንበር ላይ የሚገኝ 84 ኪሎ ሜትር ርዝመትና 66 ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው ጣና ቂርቆስን፣ ደጋ ዴሴትን፣ ደቅ ደሴትን ጨምሮ21 ሌሎች ደሴቶችን የከበበ ትልቁ የኢትዮጵያ ሃይቅ ነው። ጣና የትልቁ አባይ ወንዝ መነሻ እንዲሁም የመገች፣ የጉመራ ወንዞች ተፋሰስ መጀመርያ ነው። ጣና በርካታ የአውሮፓ ሰዎችን የነጇምስ ብሩስን ቀልብ ጭምር የሳበ የኢትዮጵያ ምስጢራዊና መንፈሳዊ ሃብት ያለበት የጻድቃን ሥፍራ ነው። በጣና ሃይቅ ደሴት የሚገኙት ቤተ ክርስትያኖች የነይኩኖ ዓምላክን፣ አጼ ዳዊትን፣ ዘርዓ ያቆብን፣ ዘድንግልን፣ አጼ ፋሲልን ጨምሮ የሌሎች በርካታ ነገስታት ዓፅም አርፎባቸዋል። ክርስትናን ወደ ኢትዮጵያ ያስገባው ፍሬሚናጦስ ዓጽሙ ያረፈውም እዚያው ጣና በሚገኘው ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስትያን ነው። ጣና ደሴት የሚገኘው ቂርቆስ ቤተ ክርስትያን ድንግል ማርያም ከግብጽ ስትመለስ እንደጎበኘችው ታሪክ ያነሳል። ጣና ቂርቆስ የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ አክሱም ከመዞሩ በፊት ያረፈበት ታሪካዊ ቤተ ክርስትያንም ነው። እንቧጭ (Eichhornia, Water Hyacinth) የተባለው ክፉ ተክል የእግዚአብሄርን ዕደ-ጥበብና ረድኤት፣ የኦሪትን ምስጢር የከበበ ሃይቅን፣ ብራናን ያጨናነቀው የነገሥታትና ካህናት ገድል የተከተበበት የኤደን ገነት ምድርን የከበበን ውሃ ለማድረቅ የበቀለ ክፉ አረም ነው። በተፈጥሮ ይሆን በተንኮል - ምክንያቱ ባልታወቀ መንገድ የበቀለውን ይህን እንቧጭ ነቃቅሎ ማጥፋት የኢትዮጵያ ሕዝብ ኃላፊነት ነው። ዛሬ አላውያን የበረቱበት የአድዋው ድል የተናቀበት ዘመን ቢሆንም እንኳን - ግድ የለም - ትንሽ ቀን ናት - እግዚአብብሄር ሁሉን በጊዜው ያስተካክላል።

ጣናን ያጎደፈውን እንቧጭ ሳነሳ እንደው እንደዘበት የአረበኞቹና ኃይማኖተኞቹ ዛሬ በሙስናው የኃጥዓን አረም የተከበቡት ትግራይ ወገኖቼ ምሬትና ሃዘን እፊቴ ድቅን አለ። መላው የኢትዮጵያ መሬት የትግራይ ምድርን ጨምሮ የደጋግና ጀግና ሕዝብ መሥፈርያ እንዲሆን ቀድሶ የወሰነው እግዚአብሄር ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ ሲወሳ መላ ሃገሪቱን ከጠላቶች በመጠበቅ ረገድ የትግራይም ልጆች አኩሪ ድርሻን ይይዛሉ። ደግም ክፉም ይሁኑ፣ የትግራይ ነገስታት - እንደሌሎች ሁሉ የኢትዮጵያን ክብር አስጠብቀዋል። ዛሬ ትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮምያ ተብሎ ከፋፋይ ዓረም ተርከፈከፈ እንጂ ጠላት ሲመጣ የኢትዮጵያ ልጆች በጠነከረው አንድነታቸው ታግዘው ወራሪን ይመልሱ ነበር። ዘንድሮ ሁሉም ተለውጧል። የሱዳን ሽማቂዎች እንኳን ጊዜ ሰጥቷቸው የኢትዮጵያን ልጆች ዘርፈው ይሸሻሉ። ሃገራችን ይህን ውርደት የተላበሰችው መርዛሙ አረም፣ ጣናን እንደከበበው እንቧጭ ያለው አድራቂ ዓረም፣ በጀግኖቹ ትግራይ ልጆች ደም ላይ ተረማምዶ ለሥልጣን የበቃ ዕለት ነው።

ህወሃት በትግራይ ሕዝብ ዙርያ የበቀለ እንቧጭ ነው። ገና ከጅምር የደደቢቱ ህወሃት ርኩስ እንቧጭ እንጂ የተቀደሰ ስንዴ ሆኖ አያውቅም። የትግራይን ሕዝብ ተጠራጣሪ አድርጎ ከሌሎች ወገኖቹ ጋር በተለይም ከአማራው ጋር እያቃረነ ጊዜ የሚገዛው ህወሃት በመሃይማን ሙሰኞች በሚመራው መከላከያና ርጎራሄ ቢስ ጨፍጫፊ አግዓዚዎች ይታገዛል። ህወሃት ለአሳፋሪ ድርጊቶች ብቻ የቆመ ለሃገር ክብር ደንታ የሌለው በቅኝ ገዥዎች የተዘራ አድራቂ እንቧጭ ነው። የህወሃት ጥፋትና ሸር እንዲህ በትንሹ ተዘርዝሮ አያልቅም። እስኪ ከህወሃት የግፍ ሥራዎች ሩቡን ያህል መዝዤ ጀግናውን የትግራይ ሕዝብ ልጠይቀው።

**ወደ ቅድስት ትግራይ መሬት ያላግባብ የሚንከባለሉ የዘረፋና የስርቆት ንብረቶችና ጥሬ ኃብቶች**

ህወሃት ከሌሎች ምድር ገንዘብ በሙስና ሰብስቡ እትግራይ መሬት ላይ ሲሚንቶ ፋብሪካና ታላላቅ ኢንዱስትሪዎች ቢገነባ ለዘራፊዎቹ እንጂ ለደሃው የትግራይ ሕዝብ ከሠማይ የወረደ መና ነው? ጀኔሬተሮችና ማሺኖች ከጎንደርና ከሌሎች አካባቢዎች ነቅሎ እትግራይ ሕዝብ መሃል ቢተክል ለትግራይ ጨዋ ሕዝብ ድምቀት ይሆናል? እንደ ቅኝ ገዢ ጠላት ሰው ሠራሽ የዘር ክልሎች ፈጥሮ አንጡራ ሃብቱን እየመነጠሩ መቀሌና አድዋ ምድር ማርከፍከፉ ለትግራይ ሕዝብ በውሃ ዳር እንደበቀለ የለመለመ መስክ የውስጥ እርካታ ሰጪ ወይንስ የነገ ስጋት? “ራስ ደጀን ተራራ የትግራይ ነው” “ወልቃይት ጸገዴ የትግራይ ነው” የሚሉት የተፋለሰ መልክዓ ምድር የተንኮል ምርምር ውጤት ወይንስ አማራን ብቀላ? ትግራይ እስክትለማ ኢትዮጵያ ትድማ” የሚለው የትግራይን ሕዝብ የማይወክለው የኃጥዓን መፈክር እውን ለተቀደስ ሕዝብ እፎይታ ነው?

**ሙስናና ገንዘብ ማሸሽ**

የሙሰኛ ባለሥልጣናት ሆቴሎች፣ መዝናኛዎች የቀማኛ ጄኔራሎች ሠማይ ጠቀስ ሕንፃዎች የትግራይን ሕዝብ እንደ ጽጌረዳ አበባ ያፈካል? በመላ ሃገሪቱ የሚገኙት የህወሃት-ኤፈርት ታላላቅ የሌብነትና ዘረፋ ንብረቶች የጀግናው ትግራይን ሕዝብ ውበት ያደምቃል? የህወሃት ባለስልጣኖች ጣራ የነካ የኃብት ክምችት ለትግራይ አማኝ ሕዝብ ምኑ ነው? የህወሃት ገዳዮች አልማዝና የከበረ ድንጋይ ለኩሩው የትግራይ ሕዝብ ምኑ ነው? ከኦሮምያ ክልል እየተዘረፈ ወደ ሼሁ ካዝና የሚዘንበው ወርቅ ለምስኪኑ የትግራይ ሕዝብ ጽድቅ ነው? የዘራፊ ህወሃቶች የውጪ ባንኮችን ያጣበበው የውጭ ምንዛሬ ለሠርቶ አደሩ የትግራይ ሕዝብ ምን ይፈይዳል? የቀማኝነትና የውንብድና ምልክቱ የመንገዶች ባለሥልጣን፣ ስኳር ኮርፖሬሽንና ሜቴክ በማንና ማን የተነደፈ ዝርፍያ ማካሄጃ ፕሮጀክት ነው? ለጋሽ ሃገሮች የሚያጎርፉትን የውጭ እርዳታ መዝብሮ ሃገርን በእዳ መዝፈቅ የትግራይንስ ሕዝብ  አያሳፍርም? ታላልቅ የሙስና ዘመናዊ ቪላዎች የከተማ ውበት ናቸው ወይንስ የሌብነት ሃውልት?

## ግድያ፣ የዘር ፍጅትና ማፈናቀል

የኦሮም ሕዝብ እስራት፣ ግድያና የእናቲቱ በልጇ ሬሳ ላይ ተቀምጦ መገረፍ፣ የቢሾፍቱው እልቂት አማኙን የትግራይ ሕዝብ አያሳዝንም? እንዳይወልዱ አምክኖ የድሆች አማሮችን ዘር ማጥፋት ለክርስትያኑና እስላሙ የትግራይ ሕዝብ ሰቀቀን አይደለምን? ገደል እየተወረወሩ ለጅብ የተጣሉ አማሮች፣ በግፍ የታረዱ ሕጻናትና እርጉዝ አማሮች፣ ከኖሩበት ቀዬ የሚፈናቀሉ አማሮች ሰቆቃና ዋይታ የትግራይን ሕዝብ አያስጨንቀውም? ደሙ ያልደረቀው የባህርዳሩና ጎንደር እልቂት ሠማዕታት አማሮች ሙታን ድምጽ እትግራይ ምድር ዘልቆ አይጮህምን? ደሃን በግብር ጫና የሚያሸማቅቀው፣ በልማት ስም የሚያፈናቅለው የሙስናው ጅራፍ የትግራይንስ ሕዝብ አይጎዳም?

## ግብረሰዶም፣ የጾታ ጥቃት፣ በሱስ መጠመድና ስደት

የግብረ ሰዶም መስፋፋት፣ በልጆች ላይ የሚደርሰው የጾታ ጥቃት፣ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ወጣቶች ሴተኛ አዳሪነት ቁጥር መናር፣ የውጣቱ ሱሰኝነት፣ በችግሩ መናር ምክንያት ተሰደው ሳለ ሰውነታቸው በአሰቃቂ ሁኔታ እየታረደ ኩላሊትና ልባቸው የሚሸጠው፣ በየባህሩ የሚሰምጡት ወጣቶች ስቃይ ኃይማኖተኛውን የትግራይ ሕዝብ «ተመስገን» ብሎ እንዲተኛ ያደርገዋል?

## የፌዝ ፖለቲካና የሃሰት የትምህርት ማስረጃ

ህወሃት በሙስና ዘፍዝፎ፣ በደም ነክሮ እንዳሻው የሚነዳቸው የአድርባዮቹ ሽር ጉድ ለትግራይ ሕዝብ አስቂኝ ድራማ ወይንስ "ወይ ጉድ" የሚያሰኝ አግራሞት? ሲጀምር ገና ደካማነታቸውን አጥንቶ የለበጣ ስም አውጥቶላቸው ለሁለት አስርት ዓመታት ተከታታይ ድራማ ማስከወኑ ከአቴንሱና ሮማው አምፊቴዓትር የተቀዳ ትወና ወይንስ ሸር የወለደው የሙስና እንቧጭ ማዳበርያ? ከአራተኛ ክፍል ማስትሬት ከስድስተኛ ክፍል ዶክትሬት የሃሳት ትምህርት ማስረጃ ማቀፍ ማንን ለማታለል?

## አሰቃቂና ዘግናኝ ድርጊቶች - ቶርች

አካላቸው በእሳት እየነደደ፣ ጥፍራቸው እየተነቀለ፣ ልብ፣ ኩላሊታቸው እየተረገጠ፣ ጭንቅላታቸው እየተፈነከተ፣ አጥንታቸው እየተሰበረ፣ በማዕከላዊ ምርመራና በየእስር ቤቶቹ አሳዛኝና ዘግናኝ ሰቆቃ የሚፈጸምባቸው እልፍ አዕላፍ አማራና ኦሮሞ ወገኖች ለትግራይ ልጆችስ ወገኖች አይደሉም? እጅና እግራቸው ታስሮ በአስቃቂ ሁኔት የሚገረፉት፣ ብልታቸው ላይ ውሃ በላስቲክ እየተንጠለጠለባቸው የሚኮላሹት፣ እርቃን ቆመው እየተሳለቀባቸው ሌት ደግሞ በባለጌዎች እየተደፈሩ የሚሰቃዩት ሴት እህቶቻችን፣ በኤሌክትሪክ የሚጠበሱት፣ አማራና ኦሮሞ ሆነው በመወለዳቸው ብቻ እላያቸው ላይ የሚጸዳዳባቸው ዜጎች እሪታና ዋይታ የትግራይን ሕዝብ አያብከነክንም? በአጋዚ ጥይት ዓረር እየተበሳ ከአማራውና ኦሮሞው ገላ ላይ የሚንቆረቆረው ንጹህ ደም የትግራይ ሕዝብስ ደም አይደለም?

## ውድ አርበኛውና ኃይማኖተኛው የትግራይ ሕዝብ

ህወሃት ፈሪሃ እግዚአብሄር በለበሰው በትግራይ ሕዝብ ዙርያ የበቀለ አንገት አስደፊ እንቧጭ ነው። ጀግናውን የትግራይ ሕዝብ በነገር አስሮ፣ በግድያ አስፈራርቶ፣ ባልተቀደስ ግምጃ፣ በዝርፍያ አልባሳት እያዘናጋ

የሚፈጸመውን ደባና ምስጢር ፈቶ እንቧጩን መመንጠር ለትግራይ ሕዝብ ዛሬ ነገ የማያስብል ታላቅ የቤት ሥራ ነው። በኢትዮጵያ ላይ ይህን የመሰለ አሳፋሪ በደል የፈጸመ መንግሥት አልታየም። ኢትዮጵያ ምናልባት አምባገነኖች እንጂ ሃገር ሻጮች፣ የቅኝ ገዥ ተባባሪዎችና በዘር ፖለቲካ እያመሱ የሚያሸብሩ ባለስልጣናት በቅለውባት አያውቅም። ኢትዮጵያ "ሕዝቡ ከአስር ዓመት በኃላ በቀን ሶስቴ ይበላል" እያለ የሚያስርብ፣ የሚያሰድድ፣ የሚያስርና የሚገድል የሸንገላ ተስፋ የሚሰጥ ልቡ በቀልን ያዘለ መሪ ቆሞባት አያውቅም። ኢትዮጵያ የራሳቸውን የሙስናና ዘረፋ ኃብት እያስመዘገቡ "ሃገሪቱ ሁለት አሃዝ እድገት አሳየች" የሚሉ ዋሾ ገዥዎችን አፍርታ አታውቅም። ኢትዮጵያን መሬቷን ለባዕድ የሚሰጡ ፈሪ መሪዎች አስተዳድረዋት አያውቁም። ኢትዮጵያ በስደተኞች ዋይታ የሚሳለቅ፣ በውጭ ባሉ ሕዝቦቿ በደል የሚደሰት፣ ስደትና ሴተኛ አዳሪነት፣ ብልግና፣ ሌብነት የሚወድ ከቅኝ ገዥዎች አስበልጦ የሚጠላት መሪ አይታ አታውቅም።

የትግራይ ሕዝብ ሆይ! በስምህ ምለው ተገዝተው ራሳቸውን እያደለቡና እያገዘፉ "የጎዳሴውን ግድብ ሙሉ ኃይል ወደ ትግራይ አዙረን ብርሃን እናንበሸብሽሃለን - ካልሆነ ካልሆነም - ታላቋ ትግራይን መሥርተን እንደ አውሮጳ በልማትና በብልጽግን እንድትኖር፣ እንደ እስራኤል የአካባቢው ልዕለ ኃይል እንድትሆን፣ ሌሎችን በብሄር፣ በጎሳና በሃይማኖት እያጫረስህ ጥሬ ኃብቱን የምትመዘብርበትን ስልት እናመቻችልሃለን" የሚሉትን ዛሬ ዙርያህን እንደ እንቧጭ ከበው የሚቀልዱብህን - ነገ አንተኑ ዙርያህን በእሳት ማግደው ሊፈረጥጡ ያሰቡትን - የጨለመ ተስፋ ሰጪ የሙስና ገዥዎችን ስብከት ፈጽሞ አትስማ። ይልቁንም የሙስናውን እንቧጭ ነቃቅለህ የእግዚአብሄርን ታላቅ ሃይል የለበስክ ፃድቅ ሕዝብና መልካም ጎሊና ያለህ መሆንህን ሳይውል ሳያድር በማሳየት የተዋረደችዋን እናት ሃገርህን እንቧዋን አብስላት።

ውድ የትግራይ ሕዝብ! ለዓመታት የዘለቀው የአማራውና ኦሮሞው የማያቋርጠው የሕዝብ ትግልና አመጽ ሊገታ እንደማይችል የሙስና ገዥዎቹም ሆነ ተባባሪዎቻቸው ጠንቅቀው ያውቁታል። እንደ ፈርዖን የደነደነው ልባቸው ቅጣታቸውን ያበዛል።

ውድ አርበኛው የትግራይ ሕዝብ! ለፍትህ፣ ነጻነትና ሠብዓዊ መብት ጥበቃ፣ ለአንድነት ሲሉ የሚማቅቁት የእነ እስክንድር ነጋ፣ አንዷለም አራጌ፣ ተመስገን ደሳለኝ፣ መራራ ጉዲና፣ በቀለ ገርባና የሌሎች እስረኞች ታላቅ ስብዕና ላንተን ወገኔ ኩራት ነው። አይዞህ ወገኔ በርታ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ